ይካ. በዚህ ፡ ዓመት ፡ ስለዝናም ፡ መዝነም ፡ ስለ ፡ በሕርና ፡ ስለ ፡ ወንዞችም ፡ መምላት ፡
ጸልዩ ። እውነተኛ ፡ አምላካችን ፡ ክርስቶስ ፡ በረከቱን ፡ ሰጥቶ ፡ እስከ ፡ ልክ
ቸው ፡ እንዲመላቸው ፤ ለምድርም ፡ ልምላሜውን ፡ ሰጥቶ ፡ ደስ ፡ እንዲያሰ
ኛት ፤ ሥጋዊን ፡ ደማዊን ፡ ሁሉ ፡ በረድኤት ፡ እንዲያጸና ፤ ለእንስሳትም ፡ ሁሉ ፡
ድኅነትን ፡ እንዲሰጥ ፡ ጸልዩ ። የኛንም ፡ ኃጢአታችንን ፡ ያስተሥርይልን ።

ይሕ. አቤቱ ፡ ይቅር ፡ በለን ።

ይካ. በጸሎታችን ፡ እናስባቸው ፡ ዘንድ ፡ አስቡን ፡ ( አትርሱን ) ስላሉን ፡ ሰዎች ፡
ጸልዩ ። እግዚአብሔር ፡ በበጎ ፡ ያስባቸው ፡ ዘንድ ፤ በየጊዜውም ፡ ይቅር ፡
ይላቸው ፡ ዘንድ ። የኛንም ፡ ኃጢአታችንን ፡ ያስተሥርይልን ።

ይሕ. አቤቱ ፡ ይቅር ፡ በለን ።

ይካ. ይህችን ፡ ሰምንት ፡ ጌታ ፡ በበጎ ፡ ይፈጽማት ፡ ዘንድ ፤ ከኛም ፡ የጠላትን ፡
መፈታተን ፡ አርቆ ፡ ሰውነታችንን ፡ እንዲያድን ፡ ይቅር ፡ እንዲለን ፡ ጸልዩ ።
ኃጢአታችንንም ፡ ያስተሥርይልን ።

ይሕ. አቤቱ ፡ ይቅር ፡ በለን ።

ይካ. ጌታችን ፡ አምላካችን ፡ ራርቶ ፡ ይቅር ፡ እንዲለን ፤ ልመናችንንም ፡ ተቀብሎ ፡ ለዚያ ፡
ለፋሲካው ፡ እንዲያበቃን ፤ የትንሣኤውንም ፡ ብርሃን ፡ በፍጹም ፡ ደስታ ፡ እዲያሳ
የን ፡ ጸልዩ ። ኃጢአታችንንም ፡ ያስተሥርይልን ።

ይሕ. አቤቱ ፡ ይቅር ፡ በለን ።